# ያውልሽ ሀብሌ

ከአብርሃም በየነ

ያባቴን የእምነት ማተብ ቃሉን፣
የፍቅራችን ቋጠሮ ውሉን፣
ላንቺ ስል የፈታሁት ሀብሉን፣
የሞትን ሸክም መቀበሌን አይቼ፣
መለያየታችን አይቀሬነቱን ገምቼ፣
የላኩልሽን የሀብሉን ምስጢር ጥቅል፣
የትግሉ ነው ህይዎቴ........ ስል፣
እንዳይበጠስ ያባቴን ስጦታ ሀብል፣
በአደራ የተውኩልሽ ለፍቅሬ መከሰቻ፣
የመለያየታችን ቦታ ይሁን ለሀዘንሽ ዳርቻ።

ስሚኝ ፍቅሬ......ፍሬህይዎት፣
ያረገዘውን ደመና ሰማዩ ድንገት፣
የበጋ ደራሽ የውሃ ሙላት ጎርፍ፣
እጣየ ካደረገው በህይዎት እንደማልተርፍ፣
ሞቴን አስቢውና ባለመኖሬ ቆርጠሽ፣
በልብሽ ውስጥ ቅበሪኝ፣
የሞት ሞቴን ተረድተሽ።

ፍሬህይዎት አብሮ አደጌ፣
የወላጆቻችን ልባዊ መፋቀር፣
የፈጠረውን ቤተሰባዊ ትስስር፣
ላለማበላሸት ስል፣
ፍቅሬን በድብቁ ይዠው ስቀር፣
በስሜቴ ቁስል ሽንቁር፣
በውስጤ ስብራት ስቃይ፣
ያቡን ደጅ አድርጌሽ ስንለያይ፣
ትናንትን ሳየው በነገው ህይዎት ሰእል፣
ህይዎትን ወደፊት ይኖሩታል፣
ግን መልሰው ይማሩታል፣
አልኩትና ራሴውኑ መራሁት ወደ ተውኔቱ፣
መኖርን ቸል ብየው፣
ማሰብ ጀመርኩ ስለ ሞቱ።

ሰማሽ እታለም ፍሬህየዎት፣
እቱ ልበልሽ ጓዲት- ፍቅረኛዬ?
ወይንስ
የቃል ኪዳኔ ማተብ የትገሌ አጋር አለኝታዬ?

ለኔ ሁሉንም ነሽ የሞት የህይዎት ባልደረባ፣
አንቺን ትቼ እኔ ወደ መሬት ስገባ፣
ያንችን ድብቅ ፍቅር አብሮ አደጌ፣
ብሞትም የኖራል በመቃብሬ ትራስጌ።

ሰማሽ ፍሬህይዎት፣
ይህን እምነት ሰንቄ ነው፣
መጓዜ ወደ እስር ቤት
የገባሁትን የቃል እዳ ልከፍል፣
የማይቀረውን ሞት ልሞት።

ስሚኝ እታለም……….
አጥንቴ ደቆ በቆዳየ ተንጥልጥሎ፣
አጥቃጥቄ ተሰባብሮ፣
ከፊል አካሌ ሰሎ፣
ስጋዬን ሳየው ተዘልዝሎ፣
አልታዘዝህ ሲለኝ እጄ፣
የኔን ሞት ብቻ ሳይሆን፣
የጓዶቼንም ጬምሬ፣
ሞትን እንድሞተው፣
ተልእኮየ አርጎት ግዳጄ፣
ዝምታዬን አከረርኩት፣
በራሴ ላይ ሞት አውጄ።

በዚህም አቋሜ ተወግጌ፣
በቀጭን ሽቦ ተገዝግጌ፣
እስከወዲያኛው ላለመነሳት ሳንቀላፋ፣
የቆምንለትን አላማ፣
የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ፣
ባንቺ ወስጥ ይዠው እኔ ስሞት፣
አንቺው አኑሪው አደራ ፍሬህይዎት።

እስከዘላለሙ አፍቃሪሽ
በላይሁን
ለምርኮኛ-ፍሬህይዎት።

ህዳር 2003